መሲሕ ተንሥአ እሙታን!

በዓቢይ ኃይል ወሥልጣን!

ዓሠሮ ለሰይጣን! አግዓዞ ለአዳም!

እምይእዜሰ፥ ኮነ ፍሥሓ ወሰላም!

በመንግሥተ እግዚአብሔር ዘለዓለም።

\+ + +

መሲሕ ከመቃብር ተነሣ!

በታላቅ ኃይልና ሥልጣን፥ እንደአንበሳ!

ሰይጣንን አሠረው! ነጻነትን ሰጠቶ ለአዳም!

ከዛሬ ጀምሮ ኾነ፥ ደስታና ሰላም!

በእግዚአብሔር መንግሥት፥ ለዘለዓለም።

\+ + +

Christ is Risen from The Dead!

In Supreme Glory and Command!

He Incarcerated The Evil Entity!

And Liberated Humanity!

Henceforth, Joy and Peace Remain!

In The Kongdom of God,

The Earthly Domain!

# ቸሩ እግዚአብሔር፣

# እንኳን፣ለ፳፻፲፫ (፪ሺ፲፫)ኛው ዓመተ ምሕረት፣

# በዓለ ትንሣኤ፣ በያለንበት አደረሰን!

**ይድረስ**፡- በምድርና በሰማያት በመላቸው፡ በኢትዮጵያ፡ **የእግዚአብሔር መንግሥት ዕቅፍ** ውስጥ፡ የእግዚአብሔርና የኢትዮጵያ ልጆች፤ ነጋሢዎችና ካህናት ኾናችሁ፥ «ኢትዮጲያ» በተባላችው የዐፅመ ርስት አገራችሁ ሠፍራችሁ፥ በኪዳናዊው ኢትዮጵያዊ የጨውነት ህልውናችሁና የመብራትነት ተልእኳችሁም፡ አልጫና ጨለማ በኾነው፡ በዓለሙ ኹሉ አህጉራት፡ በመለኮታዊው ዕቅድ ተዘርታችሁና ተሠራጭታችሁ፤ ተልካችሁና ተመድባችሁ፡ በቀዳማዊቷ የትንሣኤና በዘለዓለማዊቷ የሰንበት ሕይወት ለምትኖሩ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ወገኖቻችን ለኾናችሁት፡ ኪዳናውያን ወንድሞችና ኪዳናውያት እኅቶች ኹሉ! በያላችሁበት!

በእግዚአብሔር አብወእም ድንግል ማርያም፥ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ እና በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ስም፣ኢትዮጵያዊውን ሰላምታችንን፡ እናቀርብላችኋላን።

ከ“በዓለ-ኢትዮጵያ” ጋር ተያይዞ የመጣውን “ዓብይ ጾምን” (ሁዳዴን)፣በዚያው መንፈስና ሥርዓት ቀጥለን፥ በዓለ ሆሣዕናንና ሕማማትንም፡ በመልካም ፈጽመን፡ እነሆ፣በእግዚአብሔር ቸርነት፡ ከበዓለ ትንሣኤ ልንደርስ ችለናል። ስለዚህ እጅግ ደስ ሊለን ይገባል።

እንዲህ፡ ኢትዮጲያዊና ኪዳናዊ ደስታችንን ከመግለጽ ጋር፡ ለእያንዳንዳችን ሕይወት፥ ለአገራችን ማንነትና ለመላው ዓለም የምንነት መታደስና ትንሣኤ፡ እውን ማረጋገጫ ስለኾነው፡ ስለሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ ትንሣኤ፥ እስከ በዓለ መንፈስ ቅዱስ ድረስ ስላሉትም በዓላት፡ የተዘጋጀውን፡ የመልእክታችንን ሓተታ አቅርበንላችኋልና፡ ተመልከቱት!

-------------------------

# ትንሣኤ/ፋሲካ

ፈጣሪያችንና ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣበትን የመታሰቢያ ዕለት፡ **<u>በዚያችው በጥንተ ቀኗ</u>**፡ እኛ ኪዳናውያን ኢትዮጵያውያንና ኪዳናውያት ኢትዮጵያት፡ በጥልቅ መንፈሳዊ የደስታ ስሜት እናከብራታለን።

ይህም፡ ያለምክንያት አይደለም፤ ይህችው ዕለት፡ ፈጣሪ፡ ሰው ኾኖ፡ ወደዚህ ዓለም የመጣበትን ዓላማ፡ ከግብ አድርሶ የፈጸመባት፥ ማለትም የሰው ልጆችን የዘር ጠላቶች ደምስሶ፡ ለእኛ፡ ዘለዓለማዊ ድልን ያቀዳጀባት፥ ይኸውም፡ ከዲያቢሎስ የአገዛዝ ባርነት አውጥቶ፡ ለእግዚአብሔር ነጻ ልጅነት፥ የኃጢአትን ቀንበር አስወግዶ፡ ለንስሓ ጽድቅ፥ የሞትን ፍዳ አጥፍቶ፡ ለዘለዓለም ሕይወት ጸጋ እንድንበቃ ያደረገባት ቀን በመኾኗ ነው።

"ፋሲካ" እየተባለ ይጠራ የነበረው፡ ይኸው የትንሣኤ በዓል፡ በአገራችን በኢትዮጵያና በእኛ፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ከሌሎቹ በዓላት ይልቅ፡ እጅግ ጥልቅ በኾነ፡ የተለየ ሃይማኖታዊ ስሜትና ታሪካዊ ይዘት ይከበራል፤ አከባበሩም፡ በዘመነ ኪዳነ ልቦና ጸንቶ የኖረው ኢትዮጵያዊው የመልከ ጸዴቅ አምልኮ ሥርዓት እንደተጠበቀ ኾኖ፡ ከዘመነ ኦሪት ጀምሮ፡ በኹለት በተያያዘ ደረጃና መልክ ሲካኼድ ኖርዋል፤ ይኸውም፡-

፩ኛ. ፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ጥንቱኑ፡ ለአዳምና ሔዋን በሰጠው የተስፋ ቃሉ፡ ወደዚህ ዓለም መጥቶ፡ በአዲሱ ኪዳነ ምሕረት፡ እውነተኛው የፋሲካ በግ በመኾን፡ በመስቀል ላይ ከመሠዋቱ በፊት፡ ለዚያ፡ ለመጨረሻውና ለዘለዓለማዊው የሰው ልጆች ደኅንነት፡ መሸጋገሪያና ጥላ የኾነ የይቅርታ ቸርነቱን፡ በኪዳነ ኦሪቱ፡ ቀደም አድርጎ፡ ለእስራኤል ልጆች በሠራው የፋሲካ ሥርዓት ሲሰጥ መቆየቱ ነው።

ያም ሥርዓት፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ የእስራኤልን ሕዝብ፡ ከፈርዖን የባርነት አገዛዝ፡ ነጻ ያወጣቸው ዘንድ፡ ሙሴን፡ በኢትዮጵያዊነት፡ ከኢትዮጵያ፡ ወደግብፅ በላከው ጊዜ፡ በአንዲት አስደንጋጭ ሌሊት ከደረሰው ታላቅ መቅሠፍት የተገኘ ነበር፤ አዎን! ጣዖት አምላኪው ፈርዖን፡ እስራኤላውያኑን ነጻ ይለቅቃቸው ዘንድ፡ እግዚአብሔር፡ በሙሴ አማካይነት፡ በአገሩ ላይ፡ የተለያየ መቅሠፍትን አከታትሎ ቢያወርድበትም፡ እምቢተኛ ልቦናውን ይበልጥ በማደንደን፡ መለኮታዊውን ትእዛዝ ተቀብሎ ለመፈጸም ፈቃደኛ አልኾነም።

ካለመፍቀዱም የተነሣ፡ በመጨረሻ፡ በየቤተሰቡ የተወለዱትን፡ ከሰው እስከእንስሳ ድረስ ያሉትን፡ የግብፃውያንን የበኵር (የመጀመሪያ) ልጆች ኹሉ የሚቀሥፍ መልአክ ሞት መጥቶ፡ የፈርዖን ዐልጋ ወራሽ በኾነው በኵር ላይ ሳይቀር፡ የግድያ ግዳጁን ከፈጸመበት መቅሠፍት የተገኘው ሥርዓት ነው።

በዚያን ጊዜ ግን፡ የእስራኤል የበኵር ልጆች፡ ከዚያ የሞት መቅሠፍት የሚድኑበትን መንገድ፡ እግዚአብሔር አዘጋጅቶ ነበር፤ ይኸውም፡ ቀሣፊው መልአክ ሞት፡ በእያንዳንዱ የእስራኤል ቤተሰብ ላይ ምንም ዓይነት ጉዳት ሳያደርስ፡ የደም ምልክትን ብቻ እያየ፡ በሰላም ያልፍ ዘንድ፡ ለዚያ ቤተሰብ ቤዛ የሚኾን፡ የመሥዋዕት በግ፡ በዚያ ቤተሰብ ታርዶ፡ የዚያ በግ ደም፡ በዚያው ቤተሰብ

የመኖሪያ ቤት በር፡ ኹለት መቃኖችና ጉበን ላይ፡ ለምልክትነት እየተረጨ እንዲቀባ፥ የዚያም ቤተሰብ አባሎች፡ የዚያን በግ፡ አጥንቱን ሳይሰብሩ፡ ሥጋውን ብቻ እየጠበሱ፡ በዚያው ሌሊት ጨርሰው እንዲበሉት፡ እግዚአብሔር፡ በሙሴ አማካይነት፡ ለእስራኤል ልጆች የሰጣቸውና እነርሱም፡ ተቀብለው የፈጸሙት ትእዛዝ ነው።

በዚያች ሌሊት፡ በግብፃውያን ላይ፡ ታላቅ ድንጋጤንና ፍርሃትን ያስከተለው የቁጣው መቅሠፍት፥ በእስራኤላውያን ላይ ግን፡ ታላቅ ደስታንና ሓሤትን ያወረደው፡ ያ፡ የእግዚአብሔር የማዳኑና የማጥፋቱ፥ የምሕረቱና የመዓቱ ኃይል፡ "ፋሲካ" ተብሎ፡ በእግዚአብሔር ሕዝብ ዘንድ፡ በየዓመቱ ሲታሰብና ሲከበር የሚኖር የዘለዓለም ሥርዓት ኾነ።

፪ኛ. ይህ "የፋሲካ ሥርዓት"፡ በኪዳነ ኦሪቱ መሠረት፡ እንዲህ፡ በየዓመቱ ሲፈጸም ከኖረ በኋላ፡ ፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ፡ የፋሲካው በግ በሚታረድባት፡ በዚችው የፋሲካ ሌሊት፡ በመስቀል ላይ ራቁቱን ተሰቅሎ፡ ደሙን በማፍሰስ፡ እውነተኛውና ዘለዓለማዊው የፋሲካ በግ ኾኖ፡ ለአንደኛውና ለመጨረሻው ጊዜ መሠዋቱ ነው።

ስለፋሲካው በግ ሥርዓት፡ እግዚአብሔር፡ ለእስራኤል ልጆች፡ በሰጠው መመሪያ ውስጥ፡ "አጥንቱን አትስበሩ!" ያለው፡ የመለኮት የትንቢት ቃል፡ በዓለም የሰላም ቤዛነቱ፡ ራሱን፡ የመጨረሻው የፋሲካ በግ አድርጎ ለሠዋው፡ ለኢየሱስ መሲሕ የተነገረ መኾኑ፡ በወንጌላዊው ዮሓንስ ተጽፎ ይነበባል፤ ይኸውም፡ እግዚአብሔር አምላክ የሚወድደውና ከሓዋርያት፡ አንዱ የኾነው፡ ይህ ዮሓንስ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም ጋር፡ ከፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ መስቀል አጠገብ ቆሞ፡ በዓይኖቹ ባየው፡ የመሰከረው ነው። አዎን! ከፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ መስቀል፡ በቀኙና በግራው ዐብረው የተሰቀሉት ወንበዴዎች፡ ስላልሞቱ፡ ከመምሸቱ በፊት፡ ከየተሰቀሉበት ሊያወርዷቸው፡ በዚያ የነበሩት ወታደሮች፡ የኹለቱንም ወንጀለኞች፡ ጭንና ጭናቸውን ሰበሩዋቸው፤ ፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ ግን፡ ቀደም ብሎ፡ ነፍሱ፡ በሰዓቷ፡ ከሥጋው ስለተለየች፡ መሞቱን ለማወቅ፡ ከወታደሮቹ አንዱ፡ "ለንጊኖስ" የሚባለው፡ ቀኙ ጎኑን፡ በጦር ከመውጋቱ በቀር፡ ከአጥንቱ፡ አንዱንም ላለመስበራቸው፡ ይኸው ዮሓንስ፡ በዚያ፡ የዓይን ምስክርነቱ በጻፈው፡ የምሥራች ዜናው አረጋግጦታል።

የምሥክርነት ቃሉም፡ እንዲህ የሚል ነው፡- "**አይሁድ ግን፡ 'መሽቷልና፥ የዚች ሰንበት ቀንም፡ ታላቅ ናትና፡ እነዚህ አስከሬኖች፡ ስለሰነበት፡ በየተሰቀሉበት አይደሩ!' አሉ፤ ጭን ጭናቸውንም ሰብረው ያወርዷቸው ዘንድ፡ ጲላጦስን ለመኑት። ወታደሮችም መጥተው፡ ዐብረውት ተሰቅለው የነበሩትን፡ የመጀመሪያውን ወንበዴ ጭን፥ የኹለተኛውንም ሰበሩ። ወደፈጣሪያችን ኢየሱስም ኼደው፡ ፈጽሞ እንደሞተ ባዩት ጊዜ፡ ጭኑን አልሰበሩም።**

ነገር ግን፡ ከወታደሮቹ አንዱ፡ የቀኝ ጎኑን በጦር ወጋው፤ ያን ጊዜም፡ ከእርሱ፡ ደምና ውኃ ወጣ። ያየውም መሰከረ፤ ምስክርነቱም፡ እውነት ነው፤ እናንተም ታምኑ ዘንድ፡ እርሱ፡ እውነትን እንደሚናገር ያውቃል። ይኽ ኹሉ የኾነው፡ ከእርሱ፡ 'አጥንቱን አትስበሩ!' ያለው፡ የመጽሓፉ ቃል፡ ይደርስ፥ ይፈጸም ዘንድ ነው።"

ያ የበጉ ደም፡ የእስራኤልን የበኵር ልጆች፡ ከመቀሠፍና ከሥጋ ሞት እንዳዳነ ኹሉ፡ ይህም፡ "ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር፡ ዘየአትት ኃጢአት ዓለም፤ የዓለሙን ኃጢአት የሚያስወግድ፡ እነሆ፡ 'የእግዚአብሔር በግ'" የተባለው፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በመስቀል ላይ ተሠውቶ፡ ባፈሰሰው ደሙ፡ እኛን፡ ከኃጢአትና ከዘለዓለም ሞት አዳነን። እኒያ፡ የእስራኤል ሕዝብ፡ በዚያን ጊዜ የታረደውን በግ፡ ደሙን፡ በቤታቸው የውጭ ደጃፍ ላይ ረጭተው በመቀባትና ሥጋውን፡ በቤታቸው ውስጥ በልተው፡ ከሰውነታቸው ጋር በማዋሓድ፡ የዚያ ቀሣፊ መልአክ ሠይፍ፡ ካስከተለው ሞት እንደዳኑ ኹሉ፡ እኛም፡ ዛሬ፡ የፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕን፡ ቅዱስ ሥጋውን በልተንና ክቡር ደሙን ጠጥተን፡ ለኃጢኣታችን፡ የዘለዓለም ስርየትን፥ ለሰውነታችንም፡ የዘለዓለም ሕይወትን እናገኛለን።

ይኽን የፋሲካውን ሥርዓት፡ እንዲህ፡ እንደኪዳነ ኦሪት፡ በየቤታችን፥ እንደኪዳነ ምህረቱ ደግሞ፡ በቤተ ክርስቲያናችን የምንፈጽም፡ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ ነን። ይህም ማለት፡ በዚህ የትንሣኤ በዓላችን፥ ለአዲስ ኪዳኑ ፋሲካችን፡ መሥዋዕት ኾኖ ቀርቦ፡ እንድንበላውና እንድንጠጣው የታዘዝነው፡ ለሥጋ ምግብነት፡ በየቤታችን የታረደውን ፍሪዳና የተጠመቀውን መጠጥ ሳይኾን፡ ለኹለንተናችን የሕይወት ምግብ ይኾነን ዘንድ፡ ከሰማይ የወረደውንና ከምድር የተገኘውን፥ እውነተኛውና ዘለዓለማዊው የፋሲካ በጋችን የኾነውን፡ የሰላማችን የኢየሱስ መሲሕን፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መኾኑን እናውቃለን። (ዘጸ. ፲፪፥ ፴፯፤ ፩-፶፩። መዝ. ፴፫፥ ፰። ዮሓ. ፲፱፥ ፴፩-፴፯።)

ስለዚህ፡ በየዓመቱ በምትመጣው፡ የትንሣኤ ሌሊት፡ የዚሁ አምላካዊ ጸጋና በረከት ተካፋዮች በመኾን፡ እንዲህ፡ በፍጹም ሥጋዊ ደስታና መንፈሳዊ ሐሤት እናከብራታለን።

## የትንሣኤ ፍጹም ደስታና ሐሤት የሚገለጽበት ሥርዓት።

አዎን! እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በዚያች የትንሥኤ ሌሊት፡ እያንዳንዳችን፡ በኢትዮጵያዊነታችን የሚሰማን ሥጋዊ ደስታና መንፈሳዊ ሐሤት፡ እውነትም፡ በቃላት ሊገለጽ ከቶ አይቻልም።

ይህም የኾነውና የሚኾነው፡ ያለበቂ ምክንያት አይደለም፤ መሠረታዊና ጽኑ የኾነ ምክንያት አለ፤ ይኸውም፡ መስከረም ፩ ቀን በሚውለው፡ በእግዝእተብሔራችን ድንግል ማርያም እና በፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ ልደት የሚጀምረው፥ የእነርሱንም

*ፈለግ በመከተል፡ ከእነርሱ ጋር፡ በሥጋና በነፍስ፥ በመንፈስም ዐብረን ኾነን የምናደርገው፡ ዓመታዊው የሃይማኖት ጉዟችን፡ በአጽዋማቱ ሠረገላነትና በበዓላቱ ምዕራፍነት እየተጠናከረና እየታደሰ መምጣቱ ነው።*

ከዚያም፡ በተለይ፡ ከዓቢይ ጾም፡ እስከሕማማቱ ዕለተ ዓርብ ስቅለቱና ሞቱ ድረስ፡ በልዩው የጾም፥ የጸሎትና የስግደት ምግባሮቻችን አማካይነት፡ ከኢየሱስ መሲሕና ከቅድስት እናቱ፡ በሥጋና በነፍስ፥ በመንፈስም ሳይለይ፡ ዐብሮ፡ ከእነርሱ ጋር ከተቀበረ በኋላ፡ በዚያች፡ የሰንበት ዘለዓለማዊነቷ በሚከሠትባት ሌሊት፡ ከእናትና ልጁ ጋር ዐብሮ ስለሚነሣ ነው።

*ያ፡ በየመኖሪያ ቤታችን የሚቀጥለው ሥጋዊ ደስታ፥ ነፍሳዊ ተድላና መንፈሳዊ ሐሤት፡ በዚያች የትንሣኤ ሌሊት፡ በቅድሚያ፡ በቤተ ክርስቲያን በሚካኼዱት፡ የጸሎት፥ የማኅሌትና የቅዳሴ ሥርዓታት፡ ተገልጾ ይታያል። የትንሣኤው ሥርዓተ በዓል፡ ካህናቱና ምእመናቱ፡ የመቅደስ መስቀሉን እየተሳለሙና እንዲህ እያሉ፡ በጋለ የደስታ ስሜት፡ በቃል በሚለዋወጡት የምሥራች አዋጅ ይጀምራል፦*

ካህናቱ፡ ***"መሲሕ ተንሥአ እሙታን!"*** *ምእመናቱ*፡ ***"በዓቢይ ኃይል ወሥልጣን!"*** *ካህናቱ*፡ ***"ዐሠሮ ለሰይጣን!"*** *ምእመናቱ*፡ ***"አግዐዞ ለአዳም!"*** *ካህናቱ*፡ ***"እምይእዜሰ!"*** *ካህናቱና ምእምናቱ* (በኅብረት)፡ ***"ኮነ ፍሥሓ ወሰላም!"***

*"**መሲሕ**፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ! በታላቅ ኃይልና ሥልጣን! ስይጣንን ዐሠረው! የሰውን ልጅ ነጻ አወጣው! ከዛሬ ጀምሮ፡ ደስታና ሰላም ኾነ!"*

*ዳግመኛም፡* ***"መሲሕ፡ ተንሥአ እሙታን! ሞተ፥ ወኬዶ ለሞት! ለእለ ውስተ መቃብር፡ ወሀብ ሕይወተ፥ ዘለዓለም ዕረፍተ!***

*"**መሲሕ**፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ! ሞቶም፡ ሞትን ድል አደረገው! በመቃብር ላሉትም፡ የዘለዓለም ዕረፍት የኾነውን ሕይወት ሰጣቸው!"*

*የሚለውን የዐዋጅ ቃል፡ በዜማ እየተቀባበሉና ታላቁን ምሥራች፡ በሐሤትና በይባቤ ድምፅ ያሰማሉ።*

ከዚያም፡ *ዲያቆኑ፡ ከዳዊት መዝሙር፡* ***"ወተንሥአ እግዚአብሔር፡ ከመ ዘንቃህ እምንዋም፤ ወከመ ኃያል፥ ወኅዳገ ወይን፤ ወቀተለ ፀሮ በድኅሬሁ።***

"እግዚአብሔር፡ ከእንቅልፍ እንደሚነቃ፥ የወይን ስካርም እንደተወው ጀግና ተነሣ!" ጠላቱንም፡ አሳድዶ ደመሰሰው!" የሚለውን፡ የባዓሉን መደበኛ ምስባክ፡ ለኹለት ጊዜያት፡ በሉዓላዊ ድምጽ ያዜማል፤ ካህናቱና ሕዝቡም፡ ከእርሱ ተቀብለው፡ ለሦስት ጊዜያት መላልሰው ያዜሙታል። (*መዝ. ፸፯፥ ፷፭-፷፮።*)

በቤተ *መቅደሱ የሚካኼደው ሥርዓተ ጸሎት እንዳበቅ፡ የቅኔ ማኅሌቱ ሥርዓት፡ "ምልጣን" በሚባለው የድጓ ዜማ፡ እንዲህ እያለ፡ በመዘምራኑ ይቀጥላል፦*

**"ዮም ፍሥሓ ኮነ! በሰንበተ ክርስቲያን፥ እስመ ተንሥአ፡ ክርስቶስ እሙታን። ቀደሳ ወአክበራ፡ እምኵሎን መዋዕል፤ አልዓላ፤ አማን፥ ተንሥአ እምነ ሙታን። ...ወዮምሰ ዓባይ ፍሥሓ በሰማያት፤ ወምድርኒ፡ ትገብር ፋሲካ፤ ተኀዊባ በደመ ክርስቶስ። ...አማን፥ በአማን፤ አማን፥ በአማን፤ ተንሥአ እምነ ሙታን፤ ተንሥአ እምነ ሙታን።**

"ዛሬ፡ በዚች በዘለዓለማዊቷ ሰንበት፡ ደስታ ኾነ! መሲሕ፡ ከሙታን ተለይቶ ተንሥቷልና። እርሷንም፡ ከዕለታቱ ኹሉ ይልቅ፡ ቀደሳት! አከበራትም! ከፍ ከፍ አደረጋት! አዎን፥ በእውነት ከሙታን ተለይቶ ተነሣ! ...ዛሬ፡ በሰማያት፡ ታላቅ ደስታ ኾነ! ምድርም፡ በመሲሕ ደም ስለታጠበች፡ ፋሲካዋን ታደርጋለች። ... መሲሕ፡ ከሙታን ተለይቶ መነሣቱ፡ እውነት ነው፤ አዎን፥ መሲሕ፡ በእውነት፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ!"

በመጨረሻ፡ ማኅሌታውያኑ መዘምራን፡ **"ትንሣኤከ ለእለ አመነ! ብርሃነከ መልአ ዲቤነ!** ትንሣኤህን በምናምን፡ በእኛ ላይ፡ ብርሃንህን ሞልቶ ታየ!" የሚለውን ወረብ ወርበው፥ በጸናጽልና በከበሮ ታጅበው እያሸበሸቡ፥ ካህናቱና ሕዝቡም፡ እያንዳንዳቸው፡ የጧፍ መብራትን ይዘው፡ በይባቤና በእልልታ፡ በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ዑደት ያደርጋሉ።

ከዚህ በኋላ፡ ካህናቱም፥ ምእመናቱም፡ ይህን የትንሣኤ ባዓላቸውን፡ አማናዊ የሚያደርጉበትን፥ አማናዊነቱንም፡ ለየራሳቸው፥ ለሰብአዊው ወገናቸውና ለፈጣሪያቸው የሚያረጋግጡበትን ሥርዓት ይፈጽማሉ፤ ይኸውም፡ በታላቅ መሥዋዕትነት ጠብቀውትና ሕያው አድርገውት ለኖሩበት፡ ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታቸው፡ መታወቂያ ማኅተምና የህልውና ዘውድ የኾነው ሰማያዊው ግብዣ፡ በመላእክት ሥርዓት ተካኺዶ፡ በሚከናወነው የቅዳሴ ጸሎት፡ በተሰናዳበት፡ በቅዱሱ ገበታ ዙርያ ተሰባስበው መቅረባቸው ነው። ከዚያም፡ ከእግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶና አማናዊው የፋሲካ በግ ኾኖ፡ በመስቀል ላይ የታረደውንና ከሙታን ተለይቶ የተነሣውን፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም "በእውነተኛው አምልኮና በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ" ኾነው ለመቀበል መብቃታቸው ነው።

"የሰንበት ጌታ" የኾነው ሰላማችን ኢየሱስ መሲሕ፡ በመቃብር ውስጥ ሳይቀር በማረፍ፡ እንደጥንታዊው አምላካዊ ትእዛዙ ያከበራትን፡ አንዲትና ብቸኛ ኾኖ የኖረችውን "ሰንበት"፡ በዚህ፡ አማናዊ ትንሣኤው፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ዘለዓለማዊት ኾና፡ በሰንበትነቷ እንድትቀጥል በማድረጉ፡ አማኞቹና አገልጋዮቹ፥ የቃል ኪዳን ሕዝቦቹና ባለአደራዎቹ የኾንነው፡ እኛ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በዚህ ዓለም፡ በሕይወተ ሥጋ በምንገኝበት ህልውናችን፡ ሞት የሌለበትን፡ የመጀመሪያውን የመንፈስ ትንሣኤ ተቀዳጅተን ለመኖር በቃን! በሰዎች ሥርዓት፡ ለኹለት ተከፍላ፡ ስትዘከር የነበረችውን፡ ያችኑ፡ አንዲቱንና የመጀመሪያዪቱን "የእግዚአብሔር ሰንበት"፡

በአንዲተ ሰንበትነቷ፡ በቀጠለችበት ዘለዓለማዊነቷ እንድንኖርባትም አስቻለን።

ስለዚህ፡ በአለንበት፡ በዚህ የዓመተ ምሕረት ዘመን፡ እስከዕለተ ምጽዓት፥ ከዚያም በኋላ በዘለዓለም የትንሣኤ ሕይወት የምንኖርባት ሰንበት፡ ያችው፡ "የእግዚአብሔር ሰንበት" ኾና የኖረችው፡ አንዲቷ ሰንበት ናት።

እውነቱ፡ ይህ እንኳ፡ በአይሁድና በክርስቲያኑ ዓለም ዘንድ፡ "ቀዳሚት ሰንበት"፥ ወይም፡ "ሰንበተ አይሁድ"፥ የጌታን ትንሣኤ ምክንያት በማድረግም፡ "ዳግሚት ሰንበት"፥ ወይም፡ "ሰንበተ ክርስቲያን" ተብለው የሚጠሩ፡ ኹለት ሰንበታት ያሉን በማስመሰል አለመኾኑን፡ እናንተም ዐውቃችሁት፥ በዚህ እውነታ የተከሠተላችሁንም የሃይማኖታችሁን ምሥጢር ተገንዝባችሁት፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የምትኖሩትን፡ የኢትዮጵያዊነታችሁን የሕይወት ጸጋ፡ እውን አድርጋችሁ ትጠቀሙበት ዘንድ እናሳስባችኋለን።

## ማዕዶት።

"ማዕዶት"፡ በግእዝ፡ "ዐደወ" = "ተሻገረ" ከሚለው ግሥ ተገኝቶ፡ "መሻገር"፥ "ሽግግር" ማለት ነው፤ "ማዶ"፥ ወይም፡ "ከወንዝ ማዶ" የሚለው ዘይቤ የተገኘው፡ ከዚሁ "ማዕዶት"፡ ከሚለው ቃል መኾኑ፡ በቀላሉ ይታወቃል።

የእስራኤል ልጆች፡ በእግዚአብሔር ተጠሪ፡ በሙሴ መሪነት፡ ቀይ ባሕርን ተሻግረው፡ ከግብፅ ባርነትና ከፈረዖን ገዢነት፥ ከእኒህ ጠላቶቻቸውም ሠራዊት ጦር እንደዳኑ ኹሉ፡ "እኛም፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ በኢየሱስ መሲሕ፡ ከዲያብሎስ ገዢነት፡ ወደእግዚአብሔር ልጅነት፥ ከኃጢኣት [ከሓሰት] ቀንበር፡ ወደጽድቅ [ወደእውነት] ክብር፥ ከሞት ፍዳ፡ ወደትንሣኤ ሕይወት ተሸጋገርን!" በማለት፡ የፋሲካ እሑድ ማግሥት የኾነውን፡ የ"ሰኞን" ዕለት፡ "ማዕዶት" ብለን እናከብረዋለን።

## ዳግማዊ ትንሣኤ።

እኛ፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች፡ ዛሬ፡ በሕይወት ሥጋ እያለን፡ በዚህ ዓለም የምንኖረው ኑሮ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ትንሣኤ፡ ለመጀመሪያው የመንፈስ ትንሣኤ በበቃንበት ሕይወት መኾኑን፡ ካለፉት ውይይቶቻችን ተረድታችሁታል። ከዚህ በኋላ፡ በዚሁ፡ በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ትንሣኤ፡ አዲስ አካልን ለብሰንና የዘለዓለም ሕይወትን ወርሰን እንድንኖርበት የተዘጋጀልን፥ በትንሣኤ ዘጉባኤ የምንነሣበት፡ ኹለተኛ ትንሣኤ መኖሩንም፡ ዐውቃችኋል። (ራእ. ፳፥ ፩-፮። ተሰ. ፬፥ ፲፫-፲፰።)

ያን፡ የመጨረሻውን ትንሣኤ ለማስታወስ፡ አማናዊና የመጀመሪያው የኾነውን፥ ዛሬ እየኖርንበት ያለውን የመንፈስ ትንሣኤያችንን ከተቀዳጀንበት፡ ከፋሲካው የትንሣኤ እሑድ ቀጥሎ ያለውን ዕለተ እሑድ፡ "ዳግማዊ ትንሣኤ" ብለን እናከብረዋለን።

ፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ፡ በፋሲካው ዓርብ ተሰቅሎና ሞቶ፥ ተቀብሮም፡ በቅዱሱ ኪዳን የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ **"ዕለተ ሰነበት፡ ዘአክበራ እግዚእነ በዕረፍቱ"** ማለትም፡ "በመቃብር ዕረፍቱ ያከበራት፡ ዕለት ሰንበት" የምትባል ሲኾን፥ በአይሁድና በክርስቲያኑ ዓለም ዘንድ ግን፡ "ቀዳሚት ሰንበት"፥ ወይም፡ "ሰንበተ አይሁድ"፥ ወይም፡ "ቅዳሜ ስዑር" በተባለችው ዕለተ ሰንበት፡ በመቃብር ዐርፎ ከቆየ በኋላ፡ ሞትን ድል አድርጎና ሙስና መቃብርን (በመቃብር መበስበስን) አጥፎቶ፡ እኩለ ሌሊት ላይ፡ ለእሑድ አጥቢያ ተነሥቷል።

ይኽን ትንሣኤውን፡ በመጀመሪያ ለማየት የበቁት፡ እውነተኞቹ ሓዋርያት እነማርያም መግደላዊት ሲኾኑ፥ ከእነርሱ ቀጥለው፡ ለዚህ ክብር የታደሉት፡ ወንዶቹ ሓዋርያት ናቸው።

ይኽ በኾነ በሳምንቱ እሑድ፡ በመጀመሪያዋ የትንሣኤ ዕለት ያልነበረው ቶማስ በተገኘበተ፡ ፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ለኹለተኛ ጊዜ፡ ለሓዋርያት ስለተገለጠላቸውና በዚያን ጊዜ፡ የቶማስን ጥርጣሬ ማስወገድ ብቻ ሳይኾን፡ በይበልጥ፡ **"ብፁዓንስ፡ እለ እንዘ ኢይሬእዩኒ፡ የአምኑኒ!"** ማለትም፡ "ሳያዩ የሚያምኑብኝ፡ በፁዓን ናቸው!" የሚለውን፥ በተለይ፡ በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ፡ በአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ ምክንያት፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ቅድሚያ ተፈጻሚነትን ያገኘው የምሥራች ቃሉን ስላሰማባት፡ ይህች እሑድ፡ "ዳግማዊ ትንሣኤ" የሚለውን ስያሜ አግኝታለች። (የሓዋ ፳፥ ፳፮-፴፱፡)

# በዓለ ዕርገት።

ፈጣሪያችን ኢየሱስ መስሕ፡ ከሙታን ተለይቶ ከተነሣ በኋላ፡ በምድር ላይ ምስክሮቹ እንዲኾኑ ለመደባቸው ደቀ መዛሙርቱ፡ አርባ ቀን ሙሉ፡ <u>ስለእግዚአብሔር መንግሥት</u> ምስጢር ሲነግራቸውና ሲያስረዳቸው፥ በሃይማኖታቸውም ሲያጸናቸው ቆየ፤ ከጥቂት ቀናት በኋላም፡ በቅዱስ መንፈሱ፡ ወደዚህ ዓለም ተመልሶ፡ ከእነርሱ ጋር ዐብሮአቸው እንደሚኾንም አበሠራቸው። ይህ እስከሚኾን ድረስ ግን፡ በኢየሩስሌም እንዲቆዩ አዝዟቸው፡ እናቱን ቅድስት ድንግል ማርያምን ዐጅበውና ከብበው ባሉበት፡ እያዩት፡ ወደሰማያት ዐረገ።

በዓለ ዕርገት፡ ይህችን ዕለት በማዝከር የምናከብርባት፥ እኛም፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን፡ በመጀመሪያው የመንፈስ ትንሣኤ ሕይወት እየኖርን ያለን፡ የትንሣኤ ልጆች ስለኾንን፥ በማሕፀንና በክርስትና ጥምቀታችንም፡ ለመጀመሪያው የመንፈስ ትንሤኤ የበቃንበትንና የታተምንበትን መንፈሳዊ አካል ሰለለበስን፡

እያንዳንዳችን፡ ጽዋችን ደርሶ፡ በዕረፍተ ሥጋ፡ ከዚህ ዓለም በምንለይበት ጊዜ፡ የመሪያችንን ፈለግ ተከትለን፡ እንዲህ፡ በአርባ ቀናችን፡ ነፍሳችን፡ ወደሰማያት የምታርግ መኾኗን የምናስታውስባት ዕለት ናት።

ይህንም፡ ፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ፡ ከሙታን ተለይቶ እንደተነሣ፡ ለማርያም መግደላዊት፡ **“ኢትልክፍኒ! እስመ ዓዲ ኢዐረግሁ ኀበ አቡየ፤ ወሑሪ ባሕቱ ኀበ አኀውየ! ወበሊዮሙ፡- ‘አዐርግ ኀበ አቡየ፥ ወአቡክሙ! ኀበ አምላክየ፥ ወአምላክክሙ!’** ገና ወደአባቴ አላረግሁምና፡ አትንኪኝ! ነገር ግን፡ ወደወንድሞቼ ኺደሽ፡ ‘እኔ፡ ወደአባቴና ወደአባታችሁ፥ ወደአምላኬና አምላካችሁም ዐርጋለሁ!’ ብለሽ ንገሪያቸው፤” ብሎ ያሰማት የመልእክት ቃል፡ ከትንሣኤው በኋላ እንዲያዩት የተዘጋጀላቸው፡ ሌላው የእግዚአብሔር ድንቅ ኃይል፡ ምን ዓይነት እንደኾነ ያመለክታል። (ዮሓ. ፳፥ ፲፯-፲፰።)

ደግሞም፡ ከሙታን ተለይቶ የተነሣው ጌታ፡ በአናቱ፡ በእግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ዙሪያ የተሰበሰቡትን፡ **“የመረጣቸውን፡ ሓዋርያትን፡ በመንፈስ ቅዱስ ካዘዛቸው በኋላ፡ እስከዐረገበት ቀን ድረስ፡ ...አርባ ቀን እየታያቸው፡ ስለእግዚአብሔርም መንግሥት ነገር እየነገራቸው፡ በብዙ ማስረጃ፡ ከሕማማቱ በኋላ፡ ሕያው ኾኖ፡ ለእነርሱ፡ ራሱን አሳያቸው። ከእነርሱም ጋር ዐብሮ ሣለ፡ ከኢየሩሳሌም እንዳይወጡ አዘዛቸው።**

**“ነገር ግን፡ ‘ከእኔ የሰማችሁትን፡ አብ የሰጠውን የተሰፋ ቃል፡ ጠብቁ! ዮሓንስ፡ በውኃ አጥምቆ ነበርና፤ እናንተ ግን፡ ከጥቂት ቀን በኋላ፡ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ!/ታጠምቃላችሁ!/’ አለ።**

**“እነርሱም በተሰበሰቡ ጊዜ፡ ‘ጌታ ሆይ! በዚህ ወራት፡ ለእስራኤል፡ መንግሥትን ትመልሳለህን?’ ብለው ጠየቁት።**

**“እርሱም፡ ‘አብ፡ በገዛ ሥልጣኑ ያደረገውን ወራትንና ዘመናትን ታውቁ ዘንድ፡ ለእናንተ አልተሰጣችሁም፤ ነገር ግን፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ፡ ኃይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌምም፥ ብይሁዳም ኹሉ፥ በሰማርያም፥ እስከምድር ዳርም ድረስ፡ ምስክሮቼ ትኾናላችህ፤’ አለ።**

**“ይህንም ከተናገረ በኋላ፡ እነርሱ እያዩት፡ ከፍ ከፍ አለ፤ ደመናም ተቀበላቸው። እርሱም ሲኼድ፡ ወደሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሣለ፡ እነሆ፥ ነጫጭ ልብስን የለበሱ፡ ኹለት ሰዎች፡ በአጠገባቸው ቆሙ፤ ደግሞም፡ ‘የገሊላ ሰዎች ሆይ! ወደሰማይ እየተመለከታችሁ፡ ስለምን ቆማችኋል? ይህ፡ ከእናንተ፡ ወደሰማይ የወጣው፡ ኢየሱስ፡ ወደሰማይ ሲኼድ እንዳያችሁት፡ እንዲሁ፡ ይመጣል!’ አሏቸው።”** የሚለው፡ የወንጌላዊው ቃል፡ ስለዕርገት ምሥጢር የተነገረውን እውነታ፡ በበለጠ ያረጋግጣል። (የሓው. ፩፥ ፩-፲፩።)

# ርክበ ካህናት።

"ርክበ ካህናት"፡ በበዓለ ትንሣኤና በበዓለ መንፈስ ቅዱስ እኩሌታ ላይ፡ ማለትም፡ ትንሣኤ በተከበረ በ፳፭ኛው ቀን፥ ወይም፡ ርደተ መንፈስ ቅዱስ ሊከበረ፡ ፳፭ ቀን ሲቀረው፡ ባለው "ዕለተ ረቡዕ" የሚውል፡ የተቀደሰ የጉባኤ ቀን ነው።

መጀመሪያ፡ በኪዳነ ልቦና ተመሥሮቶ፥ በመካከሉ፡ በኪዳነ ኦሪት በተጠናከረው፥ በመጨረሻም፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ በተፈጸመው፡ በኢትዮጵያ ሥርዓተ መንግሥት፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ምልክናውና በቤተ ክህነቱ ዘርፎች ውስጥ፡ በምርጫም ኾነ፡ በመደበኛነት የሚያገለግሉት ኹሉ፡ "ካህናት" ይባላሉ፤ "የእግዚአብሔር መንግሥት አገልጋዮች" ማለት ነው። እነዚህ ኹሉ፡ በታላቁ ጥንታዊ ጉባኤያቸው፡ በአንድነት ተሰብስበውና በማናቸውም ወቅታዊ ጉዳይ ላይ ተመካክረው ውሳኔ ይሰጣሉ። ያን ኢትዮጵያዊ ሥርዓት ለማዘከር፡ ይህ ዕለት፡ **"ርክበ ካህናት"** ተብሎ፡ በበዓል መልክና በተቀደሰ ስብሰባ ይከበራል።

ይኸውም፡ ሐዋርያት፡ ቀደም ብሎ፡ እስከዕርገት፡ በፈጣሪያችን በእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ ሊቀ መንበርነት፥ ከዕርገት በኋላም፡ በመንፈስ ቅዱስ ሰብሳቢነት፡ እግዝእተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም በተገኘችበት፡ ያደረጉት የነበረውን ስብሰባ የመሰለ ነው።

# በዓለ መንፈስ ቅዱስ።

# (በዓለ ሃምሳ)

እግዚአብሔር፡ በዘመነ ብሉይ፡ በሃይማኖታቸውና በምግባራቸው ላስደሰቱት፡ ለአብርሃም፥ ለይስሓቅና ለያዕቆብ፡ በቃል ኪዳን የሰጣቸውን ተስፋ ሊፈጽም፡ የእስራኤልን ሕዝብ፡ በታላቅ ክንዱ፡ ከግብፅ አውጥቶ፡ ምድረ ከነዓንን ካወረሳቸው በኋላ፡ ሕዝቡ እንዲያከብራቸው፡ ያዘዛቸው፡ ሦስት ታላላቅ የዓመት በዓላት ነበሩ። ከእነዚህ በዓላት መካከል፡ ሦስተኛውና የመጨረሻው፡ "በዓለ ሃምሳ"፥ ወይም፡ "በዓለ ሠዊት"፥ ወይም፡ "የእሸት በዓል" ነው። የመጀመሪያው በዓል፡ "በዓለ ናእት"፥ ወይም፡ "የቂጣ በዓል"፥ ወይም፡ "የፋሲካ በዓል" ሲኾን፡ ኹለተኛው በዓል ደግሞ፡ "በዓለ መጸለት"፥ ወይም፡ "የዳስ በዓል" የሚባለው ነው።

"በዓለ ፋሲካ"፡ የእስራኤል ልጆች፡ ተጨቁነው የኖሩበት፡ የባርነት አገዛዝ አብቅቶ፡ ከግብፅ ምድር፡ ነጻ ያወጣቸውን፡ የእግዚአብሔርን የማዳን ኃይሉን፡ በዚህ ዕለት፡ ለመሥዋዕትነት አርደው በሚበሉት የበግ ደም፡ የሚያስታውሱበት በዓል ነው።

"በዓለ መጸለት"፡ እግዚአብሔር፡ የእነዚህኑ ሕዝብ፡ ሃይማኖትና ምግባር ሊፈትን፡ በድንኳን ብቻ እንዲኖሩ አደረገ፡ ለአርባ ዓመታት፡ በሲና ምድረ በዳ በመንከራተት የኖሩበትን የስደት ጉዞ እንዳይዘነጉ፡ በውጪ በሜዳ፡ ዳስ ሠርተው እንዲያከብሩት ያዘዘው በዓል ነው።

“በዓለ ሃምሳ”፡ የሕዝቡ ወገን የኾነው፡ እያንዳንዱ ሰው፡ እግዚአብሔር፡ አዘጋጅቶ ከሰጠው ነፃ አገርና ለምለም ምድር፡ በየዓመቱ፡ ሠርቶ ካመረተው ሰብሉ፥ ወይም፡ ሀብቱ ላይ፡ “በኵራቱን”፡ ማለትም፡ የመጀመሪያውን ፍሬ፡ ለበረከት በማቅረብ፡ ይህን ቸርነት ያደረገለትን ፈጣሪውን የሚያመሰግንበት በዓል ነው። (ዘሌዋ. ፳፫፥ ፩-፵፬።)

እነዚህ ሦስት ታላላቅ የእግዚአብሔር በዓላት፡ በዘመነ ሐዲስ፡ በድንግል ማርያምና በኢየሱስ መሲሕ በተገኘው ኪዳነ ምሕረት፡ ታድሰውና ተሸልመው፡ እውነተኞቹ እስራኤል በኾኑት የኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ በአዲስ ኪዳኑ በዓላት ተተክተው ይከበራሉ። እነዚህም፡ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

“በዓለ መጸለት”፡ በ“ጥምቀት በዓል” ተተክቷል። ይህም፡ ካህናት ተሸክመውና ሕዝቡ ዐጅበው፡ ወደወንዙ ውኃ በሚያወርዱት፥ በዚያም፡ ዳስ ሠርተው በሚያሳድሩት ታቦታቸው የተመሰለውን፥ መንፈስ ቅዱስም፡ በርግብ አምሳል፡ በራሱ ላይ ረብቦ የታየበትን ኢየሱስ መሲሕን፡- **“ዝንቱ ውእቱ ወልድየ፡ ዘአፈቅር! ዘቦቱ ሠመርኩ!”**

“በእርሱ ደስ የሚለኝ፡ የምወድደው ልጄ፡ ይህ ነው!” በሚል ቃል፡ ድምፁን ከሰማያት ያስሰማለት እግዚአብሔር አብ፡ ወላዲነቱና እሥራፂነቱ፡ በምስጢረ ሥላሴ የተገለጸበት አስተርእዮው፡ በማኅሌት የሚወደስበትና በቅዳሴ የሚመሰገንበት በዓል ነው። (ማቴ. ፫፥፲፯።)

“በዓለ ፋሲካ”፡ በ“ትንሣኤ በዓል” ተተክቷል። ይህም የኾነው፡ አማናዊው የፋሲካ በግ ኾኖ፡ በመስቀል ላይ ተሰቅሎና ደሙን አፍስሶ፥ ሞቶና ተቀብሮ፡ ዲያብሎስንና ኃጢኣትን፥ ሞትንና ሲኦልን ድል ነሥቶ፡ ከሙታን ተለይቶ በተነሣው፡ በኢየሱስ መሲሕ “ትንሣኤ” ነው።

“በዓለ ሃምሳ”፡ በ“በዓለ መንፈስ ቅዱስ” ተተክቷል። ይህም፡ **“‘በዓለ ሃምሳ’ የተባለው ቀን በደረሰ ጊዜ፡ ኹሉም ሓዋርያት፡ በአንድ ልብ ኾነው፡ ዐብረው ሣሉ፡ ድንገት እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ፡ ከሰማይ ድምጽ መጣ፤ ተቀምጠው የነበሩበትንም ቤት ኹሉ ሞላው። እንደእሳትም የተከፋፈሉ ልሳኖች ታዩዋቸው፤ በእያንዳንዳቸውም ላይ ተቀመጡባቸው። በኹሉም፡ መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው። መንፈስም፡ ይናገሩ ዘንደ እንደሰጣቸው፡ በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር።”** በሚለው፡ የወንጌላዊው ቃል ተረጋግጧል።

ወንጌላዊው ሉቃስ፡ በ“በዓለ ሃምሳ” ስለኾነው ዕፁብ ድንቅ ነገር፡ የገለጸውን፡ ይህን ዜናውን በመቀጠል፡

**"ከሰማይ በታች ካሉ ሕዝብ ኹሉ፤ በጸሎት የተጉ አይሁድ፡ በኢየሩሳሌም ይኖሩ ነበር፤ ይህም ድምፅ በኾነ ጊዜ፡ ህዝቡ ኹሉ ተሰበሰቡ፤ እያንዳንዱም፡ በገዛ ቋንቋው ሲናገሩ ይሰማ ስለነበር፡ የሚሉትን አጡ፤ ተገርመውም፥ ተደንቀውም፡ እንዲህ አሉ፦ 'እነሆ፥ እነዚህ የሚናገሩት ኹሉ፡ የገሊላ ሰዎች አይደሉምን? እኛም እያንዳንዳችን፡ የተወለድንበትን፡ የገዛ ቋንቋችንን፡ እንዴት እንሰማለን?"** ሲሉ ጽፏል።

*አያይዞም፡ የእነዚህን ሕዝብ ማንነት፡ ኹሉንም፡ በያገራቸው ስም እየለየ ሲዘረዝር፡ ከአይሁድ አስቀድሞ፡ በኪዳነ ልቦና፡ የአምልኮተ እግዚአብሔር አገር የኾነችውን፡ የኢትዮጵያን ስምና ብሔራዊ ቋንቋ ብቻ ሳያወስ በመቅረቱ፡ የኪዳነ ኦሪቱ ማዕከል ለኾነችው፡ ለታቦተ ጽዮን ታማኝ ባለአደራዎች የኾኑት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትይጵያውያት፡ በዚያ በዓል ላይ አለመኖራቸውን ማመልከቱ መኾኑ ይታወቃል።*

*ይኹን እንጂ፡ ወንጌላዊው፡ ለዚህ የዜና አቀራረቡ፡ በቂ ምክንያት አለው። ይኸውም፡* **"እስመ ርኢከኒሁ አመንከኒ! ብፁዓንስ፡ እለ እንዘ ኢይሬእዩኒ፡ የአምኑኒ!**

*"አንተ፡ ስላየኸኝ አመንህ፤ 'ብፁዓኑ' ግን፡ ሳያዩ የሚያምኑብኝ ናቸው" ላለው፡መለኮታዊ ቃሉ፡ የበቁ ኾነው፡ ለዓለሙ ኹሉ፡ በቀዳሚ አርአያነት እንዲያገለግሉት ያዘጋጃቸው፡ የኢትዮጵያ ልጆች መኾናቸውን፡ ሊያመለክት በመፈለጉ መኾኑ ግልጽ ነው።*

እኒያ፡ የተለያዩ ቋንቋ ያላቸው፡ የአይሁድ ሃይማኖት ተከታዮች የኾኑት ሕዝብ ኹሉ፡ እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች የለገሠውን፡ የመጨረሻውን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በዚች ዕለት፡ በዓይናቸው አይተው እንዲያምኑ የኾነው፡ ልክ፡ የእግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን ትንሣኤ፡ በገሃድና በግዘፍ አይተው እንዳመኑት፡ እንደሓዋርያት፥ ይልቁንም፡ ከእነርሱ፡ እንደአንዱ እንደኾነው፡ እንደቶማስ፡ "በማየት" ነበር። (ዮሓ. ፳፥ ፲፱-፳፱።)

*ይህ እውነታ፡ ምንም ዓይነት የሚታይ ምልክት፥ ወይም የሚጨበጥ ማስረጃ ሳያስፈልገው፡ በመንፈስ ቅዱስ ተመርቶ፡ በእጁ ካለው፡ ከቅዱስ መጽሓፉ ባነበበውና ከሓዋርያው ፊልጶስ አንደበት በሰማው የምሥራቹ ቃል ብቻ አምኖ፡ ወዲያው በተጠመቀው፡ በዚያ "አቤሜሌክ" በተባለው፡ ኢትዮጵያዊ ጃንደረባ ሃይማኖታዊ ምግባር፡ እውን ኾኖ መፈጸሙን፡ ወንጌላዊው፡ አከታትሎ በገለጸው ዜናው፡ በይፋ አሳውቋል። (የሓዋ. ፰፥ ፩-፲፩፤ ፰፥ ፳፮-፵።)*

*ፈጣሪያችን ኢየሱስ መሲሕ፡* **"ወአነሂ እብለክሙ፦ 'ሰአሉ! ወይትወሀበኩም። ጐድጒዱ! ወይትረኀወክሙ። ኅሥሡ! ወትረክቡ። እስሙ ኵሉ ዘሰአለ፡ ይነሥእ። ወዘሂ ኀሠሠ፡ ይረክብ። ወለዚሂ ጐድጐደ፡ ይትረኃዎ።'**

"እኔማ እላችኋለሁ:- 'ጠይቁ! ይሰጣችሁማል። መዝጊያን አንኳኩ! ይከፈትላችሁማል። ፈልጉ! ታገኙማላችሁ። የሚጠይቅ ኹሉ፡ ይቀበላልና። የሚፈልግም፡ ያገኛል። መዝጊያውንም ለሚያንኳኳ፡ ይከፈትለታል።" ሲል፡ ለደቀ መዛሙርቱ ስለጸሎት፡ በብዙ ምሳሌ ካስተማራቸው በኋላ፡ በመጨረሻ ያሰማቸው፡ **"ወሶበ አንትሙ፡ እንዘ እኩያን አንተሙ፤ ተአምሩ፡ ሠናይ ሀብተ ውሂበ፡ ለውሉድክሙ፤ እፎ ፈድፋደ፡ አቡክሙ ዘበሰማያት፡ ይሁብ ሠናይ፡ ሀብተ-መንፈስ ቅዱስ፡ ለእለ ይስእልዎ!?**

"እንኪያስ፡ እናንተ፡ ክፉዎች ስትኾኑ፡ ለልጆቻችሁ፡ መልካም ስጦታን መስጠትን ካወቃችሁ፡ በሰማይ ያለው አባታችሁ፡ ለሚጠይቁት፡ እንዴት አብልጦ፡ የመንፈስ ቅዱስን ሀብት ይስጣቸው!?" ብሎ የደመደመው ቃሉ፡ በዚች ዕለት መፈጸሙ፡ ይፋ ኾኖ ተጀመረ። (ሉቃ. ፲፩፥ ፱-፲፫።)

አዎን! እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች ሊሰጥ ያዘጋጀው፡ የመጨረሻው ጸጋ፡ ሥጋዊው ገንዘብና ሀብት፥ ዕውቀትና ጥበብ፥ ኃይልና ክብር ሳይኾን፡ ከእነዚህ ኹሉ የሚበልጥና የሚሻል፥ እንዚህ ኹሉ በረከቶች፡ አስቀድመው፡ በሥነ ፍጥረት፡ ከፈጣሪ፡ ተትረፍርፈው፡ ለሰው ልጆች፡ በነጻ የተሰጡ መኾናቸውን የሚገልጽ፥ ካገኙት የማይታጣ፥ ማንም፡ ሠርቆ፥ ወይም፡ ነጥቆ ሊወስደው የማይቻል፡ ሌላ፡ ረቂቅ ስጦታ መኾኑ፡ በዚች ዕለት፡ በእርግጥ ታወቀ!

አዎን! እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች፡ ሊለግሥ ያዘጋጀው፡ የመጨረሻው ጸጋ፡ ከእነዚህ፡ ከምድራውያኑ ሀብታት ይልቅ፡ እጅግ የሚጠቅመው፥ በብዛት ሊቆጠርና በመጠን ሊሠፈር፥ በክብደት ሊመዘንና በዋጋ ሊተመን የማይቻለው፡ ልዩውና ዘለዓለማዊው ገንዘብና ሀብት፥ ዕውቀትና ጥበብ፥ ኃይልና ክብር መኾኑ፡ በዚች ዕለት፡ እውን ኾኖ፡ በገሃድ ታየ።

ያ፡ በዚያች ዕለት፡ በእርግጥ የታወቀው፥ እውን ኾኖም፡ በገሃድ የታየው፡ እግዚአብሔር፡ በለጋሥነቱ፡ ለሰው ልጆች የሰጠው፡ የመጨረሻው ጸጋው፡ መንፈስ ቅዱስ ነው።

በዘመነ ብሉይ ኪዳን፡ በመከሩ ወራት ከሚውለው፡ ከ"በዓለ ሠዊት" በኋላ፡ ሰባት ሱባኤ፡ ማለትም፡ ሰባት ሳምንት ተቆጥሮ፡ ባለው ማግሥት፡ የሚውለው ሰንበት፡ "በዓለ ሃምሳ"፥ ወይም፡ በግሪክኛ፡ "ጴንጠቆስጤ" ተብሎ ይከበር እንደነበረ ኹሉ፡ እንዲሁ፡ በዘመነ አዲስ ኪዳንም፡ ከ"በዓለ ትንሣኤ" በኋላ፡ ሰባት ሱባኤ፡ ማለትም፡ ሰባት ሳምንት ተቆጥሮ፡ ባለው ማግሥት፡ የሚውለው ሰንበት፡ "በዓለ መንፈስ ቅዱስ"፥ ወይም፡ በግሪክኛ፡ "ጳራቅሊጦስ" ተብሎ የሚከበር ኾኗል።

ይኽ ቀን፡ በእግዚእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም፡ ምሥዋዐ-መድኃኒትነት እና በእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ የሰላመ-መስቀሉ ቤዛነት፡ በተገኘው ጸጋ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ በሰዎች ላይ፡ በምልዓት ወርዶ ሲያድር የታየበት ዕለት ነው። ለዚህ ጸጋ የተጠሩትና የታደሉትም፡ በቅድሚያ፡ በእግዘተብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም መሪነት፡ ከቅዱሳቱ ጋር፡ ፻፳ቱ ሐዋርያት ናቸው።

እግዚአብሔር፡ በመለኮታዊ ዕቅዱ፡ ለሰው ልጆች፡ በነፍስ ወከፍ ሊሰጥ ያዘጋጀወን፡ የዘለዓለማዊ ሕይወት ጸጋ፡ ከፍጹምነት ደረጃ ያደረሰው መኾኑን፡ በዚህ ዕለት፡ ባደረገው ችረነቱ ስላረጋገጠ፡ እነሆ፡ **"በዓለ መንፈስ ቅዱስ"፡ የዓመቱ በዓላት ኹሉ፡ ዘውድ ኾነ።**

ስለዚህ፡ የበዓላቱ ኹሉ ርእስና መደምደሚያ የኾነውን፡ ይህን ቀን፡ እኛ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በእግዚአብሔር የእውነትና የመንፈስ አምልኮ ኾነን፡ በጠለቀና በመጠቀ ፍጹም የደስታ ስሜት እናከብረዋለን።

እንግዴህ፡ ከ"መርዓዊ" ዕለተ እሑድ ጀምሮ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ በሰዎች ላይ መውረዱ፡ ለመጀመሪያ ጊዜ፡ ለዓለሙ፡ በይፋ እስከተገለጠባት እስከዚች፡ እስከዘለዓለማዊቷ ሰንበተ እሑድ ድረስ ባሉት ወራት፡ የኢትዮጵያው ሰውነት፡ የሚገኝበት ኹኔታ፡ በዓመቱ የዕድሜ ዑደቱ ጊዜ፡ በሚሰማው የህልውና ስሜት አይነት ይኾናል፤ ይህም ስሜት፡ የኢትዮጵያው ሰውነት፡ አኹን፡ በሕይወተ ሥጋ እያለ፡ በሕይወተ ነፍሱ ጭምር፡ ከድንግል ማርያም እና ከኢየሱስ መሲሕ ሳይለይ፡ በእውነትና በመንፈስ፡ ዐብሮ ባሳለፈው የትንሣኤ ሕይወት ጉዞ ተንጸባርቆ ይታያል።

ይህም፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በፍጹም መታመን እንደሚጋደል፡ ቆራጥ አርበኛ፡ ለአርባ ቀንና ለአርባ ሌሊት፡ ከዲያብሎስ እየተፈተነ፡ በገዳመ ቆሮንቶስ ካሳለፈው ጾም ጀምሮ፡ አያሌዎቹን የመስቀል ሥቃዮች ተቀብሎ፡ እስካረፈባት፡ እስከሕማማት ዕለተ ዓርብ ድረስ፡ ዐብሮት በመዋረድ፥ በመታሠር፥ በመራቆት፥ በመገረፍ፥ የእሾህ አክሊልን በመቀዳጀት፥ በመሰቀል፥ በመሞት፥ በጦር ተወግቶ ደሙን በማፍሰስ፥ በመቀበር፥ በመነሣትና በማረግ፡ ያ፡ የወንዱም፥ የሴቷም ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ በእውነትና በመንፈስ ቅዱስ፡ የእግዝእተብሔር እም፡ ድንግል ማርያም እና የእግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መስሒ ጽዋ ተሳታፊ ለመኾን በመብቃቱ ማለት ነው።

\+ + +